በኮቪድ-19 ክትባት ጥናቶች ውስጥ ብዝኃነት

062421 AMHARIC



ክትባቶች እንዴት እንደሚሞከሩ

የኮቪድ-19 ክትባቶችን ጨምሮ ሁሉም ክትባቶች ለሕዝብ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት ለደኅንነት አስተማማኝ መሆናቸውን እና በሚገባ የታለመላቸውን ሥራ እንደሚሠሩ ለማረጋገጥ ተከታታይ ጥናቶች እና ማረጋገጫ ፍተሻዎች ይደረጉባቸዋል።

እነዚህ በሐኪም ቤት ደረጃ የሚደረጉት ሙከራዎች የተለያዩ ብዝኃነት ያላቸውን ሰዎች ማካተት መቻላቸው አስፈላጊ ነው። ተመራማሪዎች ክትባቱ ለሁሉም የሰው ልጅ ቡድኖች ለደኅንነታቸው አስተማማኝ እና የታለመለትን ሥራ እንደሚሠራ ለማረጋገጥ በቂ የሆነ መረጃን ማግኘት ያስፈልጋቸዋል። ነጭ ያልሆኑ ማኅበረሰቦች በበሽታው ከፍተና ጉዳት ይደረሰባቸው እንደመሆኑ እና ክትባቱ ማኅበረሰቦች ወደፊት እንደ ማኅበረሰብ ለመቀጠል እንዲችሉ ይህ ሁኔታ በተለይ ለኮቪድ-19 በጣም አስፈላጊ ነው።

እንደኔ ባሉት ሰዎች ላይ ተሞክረው ነበር?

ከእርስዎ ዘር ወይም ብሔር ወይም እንደ እርስዎ ተመሳሳይ የጤና ችግር ባለባቸው ሰዎች ላይ ኮቪድ-19 ክትባቶች ተሞክረው እንደሆነ ሊያሳስብዎት ይችል ይሆናል።

ነጭ ካልሆኑ፣ በተለይ እነዚህን ክትባቶች መውሰዱ ጉዳይ ሊያስጨንቅዎት ይችል ይሆናል። ከዚህ ቀደምም ሆነ አሁን በሕክምና አሰጣጥ ላይ ያለ ዘረኝነት የአደባባይ ምስጢር ነው። እነዚህን ክትባቶች እና ክትባቶቹን ያዘጋጁትን ከዚህ ቀደም በእርስዎ ማኅበረሰብ እምነት ያጡትን ሥርዓቶች ሊያምኗቸው ይችሉ እንደሆነ ራሱ ሊያሳስብዎት ይችል ይሆናል።

እምነትን ዳግመኛ መገንባት

እነዚህ ክትባቶች የ Emergency Use Approval (EUA) /የድንገተኛ ጊዜ የመጠቀም ፈቃድ/ ከ Food and Drug Administration (FDA) / ከምግብ እና መድኃኒት ቁጥጥር አስተዳዳሪ በአሜሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፈቃድ አግኝተዋል — እነዚህም Pfizer/BioNTech፣ Moderna እና Johnson & Johnson ክትባቶች ናቸው። በመላው ዓለም ከመቶ የሚበልጡ ተጨማሪ ክትባቶች በተለያየ የዝግጅት ደረጃ ላይ ናቸው። ተጨማሪ ክትባቶች ወደፊት የሚፈቀዱ ይሆናሉ።


ለኮቪድ-19 ክትባቶች፣ ተመራማሪዎች የማኅበረሰቦችን እምነት ለማግኘት እና ለጥናታቸው የሚጠቀሙባቸውን ብዝኃነት ያላቸውን በጎ ፈቃደኞች ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በዘር፣ በብሔር፣ በዕድሜ እና እንዲሁም በተለያዩ የጤና ችግር ያለባቸውን የተለያዩ ሰዎችን አካተዋል። ጥናቶቹ ከዚህ ቀደም በሌሎች የክትባት ጥናቶች ላይ ከነበሩ ብዝኃነቶች ይልቅ ይበልጥ ብዙ ዓይነት ሰዎችን ያካተቱ በመሆን ተጠናቀዋል። በጥናቶቹ ላይ የተለያዩ ሰዎች ተቀላቅለው የተሳተፉት፣ አጠቃላዩ በአሜሪካ ያለ የሰው ዓይነት በሙሉ የተካፈለባቸው አስመስለዋቸዋል።

የ Pfizer ክትባት ጥናቶች

በደረጃ 3 **ጥናት ላይ ያሉ ሰዎች ድምር - ወደ 45,000 ሰዎች**

ከአሜሪካ ተሳታፊዎች መካከል 30% ገደማ የሚሆኑት ራሳቸውን ነጭ እንዳልሆኑ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው (በዓለም ዙሪያ 44% ይደርሳሉ)።





(ዓለም አቀፍ የዘር እና የብሔር ምድቦች በጥናቶቹ ሪፖርት በተደረገው መሠረት።)


ወደ 46% የሚሆኑት ቅጥ ያጣ ውፍረት፣ የስኳር በሽታ፣ እና የሳንባ በሽታ ጨምሮ የኮቪድ-19 በሽታን ሊያወሳስበው የሚችል ቢያንስ አንድ የጤና ችግር ነበረባቸው። የጥናቱ ተሳታፊዎች ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 56+ ነበር።

የ Moderna ክትባት ጥናቶች

በደረጃ 3 ጥናት ላይ ያሉ ሰዎች ድምር - ወደ 30,000 ሰዎች

37% ገደማ የሚሆኑት ራሳቸውን ነጭ እንዳልሆኑ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው።





(የዘር እና የብሔር ምድቦች በጥናቶቹ ሪፖርት በተደረገው መሠረት።)

ወደ 22% የሚሆኑት የስኳር በሽታ፣ ቅጥ ያጣ ውፍረት፣ የልብ በሽታ፣ የሳንባ በሽታ እና የጉበት በሽታ ጨምሮ የኮቪድ-19 በሽታን ሊያወሳስበው የሚችል ቢያንስ አንድ የጤና ችግር ነበረባቸው።


የጥናቱ ተሳታፊዎች ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 65+ ነበር።

የ Johnson & Johnson ክትባት ጥናቶች

በደረጃ 3 ጥናት ላይ ያሉ ሰዎች ድምር - ወደ 44,000 ሰዎች

ከአሜሪካ ተሳታፊዎች መካከል 35% ገደማ የሚሆኑት ራሳቸውን ነጭ እንዳልሆኑ አድርገው የሚቆጥሩ ናቸው (በዓለም ዙሪያ 76% ይደርሳሉ)።





(የዘር እና የብሔር ምድቦች በጥናቶቹ ሪፖርት በተደረገው መሠረት።)

ከተሳታፊዎች መካከል ወደ 41% የሚሆኑት ደም ግፊት፣ ስኳር በሽታ እና ቅጥ ያጣ ውፍረት ጨምሮ የኮቪድ-19 በሽታን ሊያወሳስበው የሚችል ቢያንስ አንድ የጤና ችግር ነበረባቸው።

የጥናቱ ተሳታፊዎች ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 65+ ነበር።

ሁሉም ሦስቱ ፈቃድ ያገኙ ክትባቶች ለደኅንነት አስተማማኝ እና ውጤታማ ናቸው። እንደ ሁሉም መድኃኒቶች ሁሉ፣ የሕክምና ከፍተኛ ባለሙያዎች ከክትባቶቹ ጋር በተገናኘ ማናቸውም ለደኅንነት አሳሳቢ የሆኑ ነገሮችን ዱካ መከታተላቸውን ቀጥለዋል። ይህንን ክትትል V-Safe በሚባለው የደኅንነት ሪፖርት አደራረግ ሥርዓት በኩል ያደርጋሉ። በዚህ መንገድ ክትባቶች በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች እየተሰጡ ባሉበት ሁኔታ በጣም ያልተለመዱ ዓይነት አሳሳቢ ነገሮችን ለማግኘት እና መፍትሔ ለመስጠት ይችላሉ።

ክትባቶች እርስዎን ጥበቃ ያደርግልዎታል እና የኮቪድ-19 ስርጭትን ይገታሉ። በተቻልዎት ፍጥነት ኮቪድ-19 ክትባትን እንዲከተቡ አጥብቀን እንመክራለን።

አካባቢያዊ መረጃን ለማግኘት በካውንቲ ድር ጣቢያዎ ላይ COVID-19 ን ይፈልጉ ።እንመክራለን

CLACKAMAS COUNTY

COLUMBIA COUNTY OREGON

Multnomah County Health Department

WASHINGTON COUNTY OREGON